# ትግላችን




**ልዩ ቁጥር** **ነሐሴ 1961**

# ትግላችን

**አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር**

**ወርሃዊ መፅሄት**

**በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ**

**በአውሮፓ የኢ.ት.ተ.ማ. የ9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ዜናዎች**


አዘጋጅ— እንዳርጋቸው አሰግድ

1 Berlin 19
Harbigstr. 1



ነሀሴ 1691 ዋጋው 1 ብር

ልዩ ቁጥር

## የመንግስቱን ጋዜጦች ስናገላብጥ

### ስደት ወይስ ክህደት

ባለፈው ወር ሰባት ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች የዘራፊዎቹን
አውሮፕላን ጠልፈው ወደ ሱዳን መግባታቸው ይታወሳል። የዚህ ጀብ
ዱ ሬቮሉሽናዊ ትርጉም የሚገባንና በጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ የነ
ፃነት ትግል ውስጥ ተገቢ ቦታውን የምንሰጠው ወጣቶች ድርጊቱን በ
አድናቆትና በታላቅ ደስታ ተቀብለነዋል።ይህን ሊሸሽግ የማይቻል ጉድ.
የመንግሰቱ ጋዜጦች እንዴት አድርገው ለህዝቡ እንደሚያቀርቡለት
ለማየት በጣም ጓጉተን ነበር። በሀገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ወጣ
ቶች እንደዚህ አይነት አዲስ የትግል ዘዴ ሲከፍቱ፣ ከተለመደው እጅ
እጅ ከሚለው ማደናቆሪያ ወጣ ብለው ይህን አዲስ ዘዴ «ለማራከስ ሲ
ሉ» አዲስ ማወናበጃ ያቀርባሉ ብለን ነበር፤ግን አልቆባቸዋል። አሁንም
ለማወናበጃ የሰነዘሯቸው እነዚያው ‹ክህደት፣የውጭ እጅ፣ከባህል ውጭ
... » ወዘተ. የሚሉ ናቸው።

ከመደጋገም የተነሳ «ከባህል ውጭ» የሚሏት እዚህም አ
ምልጣቸው ስለነበር በጣም ሳቅን።ለምሳሌ ያህል ሄራልድ የተባለው ጋ
ዜጣ ሲዘባርቅ ‹እንደዚህ አይነቶቹ ድርጊቶች በፍፁም ከባህላችንና ከ
ልማዳችን ውጭ ናቸው» ይላል። የትኛው ነው ከባህል ውጭ ? ድፍረ
ቱና ጀግንነቱ እንደሆነ በባህላችን ያለ ነው። አውሮፕላን መጥለፍ እን
ደሆነ፣ መቸስ ድሮስ ቢሆን በምን ፈሊጥ ከባህላችን ውስጥ ይግባ ? አ
ውሮፕላን አገራችን የገባው ትላንትና፣ባህላችንና ልማዳችን የምንለው
የብዙ ዘመናት ! ታዲያስ ከባህላችን ውጭ አይሆንሳ እንዴት ይሁን ?!

በዚህ ጉዳይ በብዙ የዘባረቀው ‹አዲስ ሪፖርተር» የተባለ
ው «ተማርን» የሚሉት ጋዜጣ ነው።ከላይ እስከታች ፍሬ ከርስኪ ነው
ሲጀምር ወጦቶቹ «አገራቸውን መርገም መርጠዋል፤እስከዚህ ድረስ ዝ
ቅ ብሎ እናት አገርን በግልፅ መስደብ በፍፁም ከኢትዮጵያዊነት ውጭ
ነው » እያለ ይተቻል።እንደዚህ አይነቱ ቅጥ ያጣ መዘባረቅ በውነቱ ተ
ማርን ከሚሉት ብእር መውጣቱ ያሳፍራል። ከህዲ መንግስትን መታገ
ልንና አገርን መክዳት ምን አንድ አደረጋቸው ? በአድራጉታቸው



የኢትዮጵያን ህዝብ የነፃነት ትግል ለአለም አስታወቁና አገር መሳደብ
ነው ? ያዋረዱትና ያጋለጡት ሀይለስላሴንና ብችሎቹን በጠቅላላው የ
ኢትዮጵያን ህዝብ ጠላቶች ነው።

ከመቸ ወዲህ ነው የገዢ ቤተሰቦችና ኢትዮጵያ አንድ የሆ
ኑት ? ከመች ወዲህ ነው ኢትዮጵያን በምናይበት አይን ነጣቂዎቹን የ
ገዢ ቤተሰቦች እንድናይ የተደረገው ? ይኸ እነዚህ ተማርን የሚሉ የ
ደረሱበት አቋም ይሆን ? እኛ ይኸን የአጨብጫቢዎች ርካሽ ሀሳብ አ
ንቀበለውም።ዛሬ አገሩን የሚወድ የህዝብ ወገን የሆነ ሁሉ እነዚህን ወ
ንበዴዎች ማጋለጥ አለበት፤ በማንኛውም ዘዴ መታገልና መዋጋት ያስ
ፈልጋል።ለነፃነት መታገል ደግሞ የሚሸሽግ ምስጢር የለውም። እርግ
ጥ ለነፃነት መታገል ሲያወጣ፣ሲያወርድ፣ሲያደክም እናውቃለን፤ሲያዋር
ድ ሲያሳፍርና ሲያሸከረምም ግን ገና ዛሬ ከናንተ መስማታችን ነው።

ከዚያም ቀጠል ያደርግና፡«እነዚህ ወጣቶች መንግስቱ፣ቤተ
ሰቦቻቸውና የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ በታላቅ መስዋእትነት እንዲያ
ገለግሉ ያስተማራቸው ናቸው» ይላል። እር
ግጥ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ በታላቅ መስዋእትነት እንዳስተማረ አይጠ
ረጠርም።የትምህርት ታክስ እየተባለም ከህዝቡ ላይ መአት ገንዘብ በየ
አመቱ ይሰበሰባል፤ ሆኖም ባሁኑ አገዛዝ ስር ለህዝቡ የሚደረገው አገ
ልግሎት ምን አይነት ነው ? እነዚህ ምሁራኖች አሁንም ተመልሰው የ
ገቡበት ማጥ ያው ነው። ህዝቡንና የገዢ ቤተሰቦችን አንድ አድርገው
ወስደዋቸዋል። በነሱ ቤት የህዝብ ሸክም በመሆን ለገጋ ቤተሰቦች ማገ
ልገል ህዝቡን እንደማገልገል ይቆጠራል፤ ከገጋ ቤተሰቦች ጋር ተዋህ
ዶ ህዝብን መበዝበዝና መጨቆን ህዝብን እንደማገልገል ይታያል። እን
ደናንት አይነቱ «ተምሮ ማገልገል» የኢትዮጵያን ህዝብ እንዳንገፈገፈ
ው አልተረዳችሁት ይሆን ? በዚህ በዝባዥ መንግስት ስር የሚቀጠቀጠ
ውን የኢትዮጵያን ህዝብ ተምረው ለማገልገል የሚፈልጉ ሁሉ ተግባሩ
ቸው ከህዝቡ ጐን ተሰልፎ መንግስታችሁን መዋጋት መሆኑን አልተረ
ዳችሁት ይሆን ?

በሌላ በኩል ደግሞ ያው የተለመደው ማንቋሸሻ አለ። ‹በተ
ገኘው ወሬ መሰረት› ይላል ይኸው ጉደኛ ጋዜጣ።«አንዳንዶቹ በፈተና

ቸው ወድቀዋል።አንዳንዶቹ ደግሞ መጥፎ ውጤት አምጥተዋል።»እንዲያው ይሁንስ ብንል፤ከመቼ ወዲህ ነው የፈተና ማርክ የሀገር ፍቅር ስሜት መለኪያ የሆነው ?ፈተና መውደቅንና አውሮፕላን ጠለፋን እንደዚህ በአስደናቂ ታእምር ከገናኛችኋቸው መጭውንም ገምታችሁ መጠንቀቅ ሊኖርባችሁ ነው። ዘንድሮ ብቻ ከስር ሽህ ተማሪዎች በላይ የዩኒቨርስቲ መግቢያውን ፈተና ወድቃችሁ ተብለዋል። ታዲያ በዚህ አያያዝ ጀቶች በዱቤም ቢሆን መፈላለጉ አይሻልም ?

መደምደሚያው ላይ፤መቼም ሰሞኑም የፍርድ ሰሞን ነውና ምስኪኖቹ ጋዜጦችም ሲፈርዱ እንደዚህ ይላሉ፡ ‹ኢትዮጵያኖች የኢትዮጵያን ብሄራዊ (!) አውሮፕላን ጠልፈዋል፤ በጠቅላላው በሀገሪቱ (!) ላይ የተፈፀመ ወንጀል (!) ነው።ወንጀለኞቹ ቱገቢውን ቅጣት መቀበል አለባቸው(!)። እንግዲህ የሚሰማ ቢገኝ መከረኛው የኢትዮጵያ ህዝብ አውሮፕላኑም ይዘረፍበት ጀመር ሊሉን ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ የየትኛው አውሮፕላን ነው ባለቤት የሆነው? የትኛው አውሮፕላን ነው የብሄሩ ሀብት የሆነው? የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአሜሪካን አየር መንገድና (TWA) ጭብጥ በማይሞሉ የገዢ ቤተሰቦች ሽርክነት ለመዝረፊያ የተቋቋመ «የንግድ መደብር»መሆኑ ተረሳ እንዴ? አገልግሎቱ የሚውለው ለነዚህ ጭብጥ የማይሞሉ ቤተሰቦችና ለTWA ባለሀብቶች ሀብት ማዳበሪያ መሆኑን እነዚህ ፈራጅ ጋዜጦች እንዴት ሊዘነጉት ቻሉ ? ቆሎ አሮበት፤ ጭብጦ ደርቆበት የሚኖረው ህዝብ ከመች ወዲህ ነው የአይሮፕላን ባለቤት የሆነው?ምንአልባት ጋዜጠኞቹ ለማለት የፈለጉት ከኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በተነጠቀው ገንዘብ የተገዛውን አይሮፕላን ማለታቸው ይሆን ?ይህን ማለታቸው እንደሁ ተማሪዎችንም አይሮፕላን ጠልፎ እስከ «መሰደድ» ያደረሳቸው ይኸው ነጠቃና ነጠቃን በዘዴ የመቃገል ፍላጎት መሆኑን ሊገነዘቡት በተገባ ነበር።

አረ ተው ቀልዱ ይቅር! የወንድሞቻችን ድርጊት ሽሽትም ክህደትም ውርደትም አይደል።ከፋሽስት ፖሊስ ጥርስ ውስጥ በጣጥሶ፤ ሰባት ሰው እንደአንድ ተማክሮ፤አንዱ አንዱን ሳይከዳ፤በእንደዚህ አይነት ደፋርነትና ቆራጥነት በሚጠይቅ ዘዴ አምልጦ የነፃነትን ትግል ጊዜና ቦታ መርጦ ለመቀጠል መሰደድ አንድ ትልቅ ጀግንነት ነው።



እናንተ ስደት ሲባል የምታውቁት የሀይለስላሴን «አጉል ስደት›ብቻ ነው መሰል? ግን በጠላት ጊዜም እኮ ስደተኞች ነበሩ።እንደነዚሁ እንደወንድሞቻችን በብሄራዊ የነፃነት ትግላችን ውስጥ ሲባክኑ ጠላት በተለይ ሲያሳድዳቸው፤መሳሪያና ስንቅ ሲያልቅቸውባ አገራቸውን ለጊዜው እየለቀቁ የተሰደዱና ጦርነቱ ሳያልቅ ተመልሰው ጠላትን በየቦታው የገጠሙት ብዙ አርበኞች ናቸው። የስደት ትርጉም ይህ ነው ወንድሞቻችን ከዚህ የተለየ የሰሩት ምንም የለ።

አንዲት ነገር እንሳሳት።ወንድሞቻችን ከአድሀሪው መንግስት ፖሊሶች አምልጠው «ቀን እስኪወጣ» እየተቀማጠሉ ለመቀመጥ አልወጡም። ይመለሳሉ።ለነፃነት መጋደል ማለት ጊዜና ቦታ ሳያማርጡ እንደእሳት ራት ከጠላት እጅ መግባት አይደለም።የአገር ፍቅር ያነደዳቸው ናቸው፤ከህዝቡ ጋር ለመዋሀድ የቆረጡ ናቸው።የትና መቼ እንደሚታገሉ የሚያውቁና ሀላፊነታቸውን በደንብ የተገነዘቡ ናቸው። ለዚህ ጥርጥር አይግባችሁ።

---